ቁጥር OFAUF-03.5/10/20
ቀን 24/05/2013

ሚኒስቴር ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለክብርት ወ/ሮ ደሚቱ ሐምቢሣ

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊና

የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የቱሪዝም ኢትዮጵያ የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 4 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 5 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሣቦችን የያዘ የሥራ አመራር ሪፖርት በድምሩ 9 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን::

ከማክበር ሠላምታ ጋር

በየነ ገብሬ
ፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክተር
Finance & Communication Oranization
Audit Director

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት *

<u>ግልባጭ:-</u>

- ለቱሪዝም ኢትዮጵያ
  (4 ገጽ ኦዲት ሪፖርት እና
  5 ገጽ የሥራ አመራር ሪፖርት
  <u>አዲስ አበባ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የቱሪዝም ኢትዮጵያ

የ2012 በጀት ዓመት ሂሣብ

ኦዲት ሪፖርት

ጥር /2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የቱሪዝም ኢትዮጵያ

የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የቱሪዝም ኢትዮጵያ የተመደበለትን የመደበኛና ካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የቱሪዝም ኢትዮጵያ ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን የዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የሂሳብ ሪፓርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የቱሪዝም ኢትዮጵያ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
የሰነድና ማህደር

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች

የቱሪዝም ኢትዮጵያ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የመ/ቤቱ አደረጃጀትና የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት በተመለከተ

መንግስት በአደረገው የአደረጃጀት ለውጥ መሰረት የቱሪዝም ኢትዮጵያ በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 በአንቀጽ 32 ተራ ቁጥር 2 መሰረት የተቋቋመ መሆኑ ይታወሳል። ይሁን እንጂ፡-

1. በድርጅቱ የማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ድርጅቱ ስለሚከተለው የግዥና የፋይናንስ አስተዳደርና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት በግልጽ ያልተገለጸ መሆኑ፡-
2. ድርጅቱ ከ2012 በጀት ዓመት በፊት የግዥና የፋይናንስ አስተዳደርና የሪፖርት አቀራረብ በተመለከተ ይገለገል የነበረው በመንግስት የሂሳብ አያያዝ መሰረት(የተቀናጀ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት /IFMIS/ የነበረ ቢሆንም በ2011 በጀት ዓመት መጨረሻ ስለነበረው ከወጪ ቀሪ(ጥሬ ገንዘብ ፤ የባንክ ሂሳብ ፤ ተሰብሳቢ ሂሳብ ፤ ተከፋይ ሂሳብ ወ.ዘ.ተ) በተመለከተ ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ ሪፖርት የሌለ መሆኑ፤
3. ድርጅቱ በአዲስ መልክ ሲቋቋም ከመንግስት በጀት ያልተመደበለት በመሆኑ የስራ ማስኬጃ በጀት ስለሌለው ስራዉን ለማከናወን እንዳልተቻለ በመግለጽ በቁጥር ተኢ/11136/2012 በቀን 5/01/2012 ዓ.ም ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር በተ9/6/1 በቀን 14/01/2012 ለ2012 በጀት ዓመት የተፈቀደ የበጀት ዝውውርና ሽግሽግ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት መስከረም 9/2012 ዓ.ም በቁጥር መ210-7/721/1 በተጻፈ ደብዳቤ ሀብት ማሰባሰብ እስኪችል ድረስ የስራ ማስኬጃ ድጋፍ እንዲደረግለት በተወሰነው መሰረት በ2012 በጀት ዓመት በሂሳብ መደብ 6412 ብር 40,000,000.00 (በፊደል አርባ ሚሊዮን ብር) እንደተፈቀደ የቀረበው መረጃ ያሳያል። ይሁን እንጂ በ2012 በጀት ዓመት ለተቋሙ በድጎማ ከተፈቀደለት በጀት ውስጥ ብር 21,424,773.03 ከገንዘብ ሚኒስቴር የተላለፈለት ቢሆንም፡-በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት፤በመንግስት ያልሆኑ ድርጅቶች የግዥና የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ወይም ተቀባይነት ባለው የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት መሰረት ሂሳቡን መዝግቦ ያልያዘ ከመሆኑ በተጨማሪ፡-

- የገቢ ሂሳብ
- የዝውውር ሂሳብ
- የወጪ ሂሳብ (በሂሳብ መደብ ተለይቶ ያልተመዘገበ መሆኑ)
- ተሰብሳቢ ሂሳብ
- የተከፋይ ሂሳብ
- የተጣራ ሃብትን
- የሂሳብ ሙከራ
- የተጣራ የሂሳብ ሙከራ ማጠቃለያ

ሪፖርት ያልተዘጋጀ መሆኑ በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከላይ በተገለፁት ጉልህና መሠረታዊ ሁኔታዎች የተነሳ የቱሪዝም ኢትዮጵያ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ትክክለኛውን ገጽታ ለማሳየቱ አስተያየት ለመስጠት አያስችልም፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

ቱሪዝም ኢትዮጵያ
የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት
የሥራ አመራር ሪፖርት

ጥር /2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

ቱሪዝም ኢትዮጵያ

የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ቱሪዝም ኢትዮጵያ የ2012 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርት ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን ቱሪዝም ኢትዮጵያ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፡

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ ሪፖርቶቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሣብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሣብ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች የማዘጋጀት ኃላፊነት የቱሪዝም ኢትዮጵያ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

የቱሪዝም ኢትዮጵያ የ2012 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች የሥራ አመራር ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የመ/ቤቱ አደረጃጀትና የፋይናንስ

1.1 የመ/ቤቱ አደረጃጀትና የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት በተመለከተ

1.1.1 ግኝት

መንግስት በአደረገው የአደረጃጀት ለውጥ መሰረት የቱሪዝም ኢትዮጵያ በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 በአንቀጽ 32 ተራ ቁጥር 2 መሰረት የተቋቋመ መሆኑ ይታወሳል። ይሁን እንጂ፡-

1. በድርጅቱ የማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ድርጅቱ ስለሚከተለው የግዥና የፋይናንስ አስተዳደርና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት በግልጽ ያተገለጸ መሆኑ፡-

2. ድርጅቱ ከ2012 በጀት ዓመት በፊት የግዥና የፋይናንስ አስተዳደርና የሪፖርት አቀራረብ በተመለከተ ይገለገል የነበረው በመንግስት የሂሳብ አያያዝ መሰረት(የተቀናጀ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት /IFMIS/ የነበረ ቢሆንም በ2011 በጀት ዓመት መጨረሻ ስለነበረው ከወጪ ቀሪ(ጥሬ ገንዘብ፣የባንክ ሂሳብ፣ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ተከፋይ ሂሳብ ወ.ዘ.ተ) በተመለከተ ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ ሪፖርት የሌለ መሆኑ፣

3. ድርጀቱ በአዲስ መልክ ሲቋቋም ከመንግስት በጀት ያልተመደበለት በመሆኑ የስራ ማስኬጃ በጀት ስለሌለው ስራዉን ለማከናወን እንዳልቻለ በመግለጽ በቁጥር ተኢ/11136/2012 በቀን 5/01/2012 ዓ.ም ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ መሰርት የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር በተ9/6/1 በቀን 14/01/2012 ለ2012 በጀት ዓመት የተፈቀደ የበጀት ዝውውርና ሽግሽግ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት መስከረም 9/2012 ዓ.ም በቁጥር መ210-7/721/1 በተጻፈ ደብዳቤ ሀብት ማሰባሰብ እስኪችል ድረስ የስራ ማስኬጃ ድጋፍ እንዲደረግለት በተወሰነው መሰረት በ2012 በጀት ዓመት በሂሳብ መደብ 6412 ብር 40,000,000.00 (በፊደል አርባ ሚሊዮን ብር) እንደተፈቀደ የቀረበው

መረጃ ያሳያል። ይሁን እንጂ በ2012 በጀት ዓመት ለተቋሙ በድጎማ ከተፈቀደለት በጀት ውስጥ ብር 21,424,773.03 ከገንዘብ ሚኒስቴር የተላለፈለት ቢሆንም፡- በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት፤በመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥና የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ወይም ተቀባይነት ባለው የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት መሰረት ሂሳቡን መዝግቦ ያልያዘ ከመሆኑ በተጨማሪ፡-

- የገቢ ሂሳብ
- የዝውውር ሂሳብ
- የወጪ ሂሳብ(በሂሳብ መደብ ተለይቶ ያልተመዘገበ መሆኑ)
- ተሰብሳቢ ሂሳብ
- የተከፋይ ሂሳብ
- የተጣራ ሃብትን
- የሂሳብ ሙከራ
- የተጣራ የሂሳብ ሙከራ ማጠቃለያ

ሪፖርት ያልተዘጋጀ መሆኑ በኦዲት ለማወቅ ተችሏል።

1.1.2 <u>ስጋት</u>

- ድርጅቱን የግዥና የፋይናንስ አስተዳደርና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት የሚገልጽ የሂሳብ አያያዝ ማኑዋል የሌለው ከሆነ እንዲሁም የድርጅቱ የፋይናንስና የስራ እንቅስቃሴ ተቀባይነት ባለው የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት መሰረት ተመዝግቦ ካልተያዘ እንዲሁም የድርጅቱን የሂሳብ እንቅስቃሴና አቋም የሚገልጹ ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርቶችና የበጀት ዓመቱ የሂሳብ መግለጫዎች የማይዘጋጁ ከሆነ የድርጅቱን የፋይናንስ እንቅስቃሴ ኦዲት ለማድረግም ሆነ በጉዳዩ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት አያስችልም።

1.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

- ድርጅቱ አጠቃላይ የሂሳብ/ፋይናንስ እንቅስቃሴውን ተቀባይነት ባለው የግዥና የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትና የሂሳብ አመዘጋገብና የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት የሚገልጽ የሂሳብ ማኑዋል በማዘጋጀት ወርሀዊ ሪፖርቶችና ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫዎች በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ማቅረብና ስለትክክለኛነቱም ኦዲት ማስደረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ተቋሙ በአዋጅ ቁጥር መቋቋሙ የሚታወስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ድርጅቱ የሚጠቀመው የግዥና ፋይናንስ አሰራር ስርዓት ለመስራት ደንብ እየተዘጋጀ በመሆኑ ለወደፊቱ የምናስተካከል መሆኑን

- በድርጅቱ ከ2011 በጀት ዓመት የግዥ ፋይናንስ አስተዳደር ሪፖርት አቀራረብ በኢፍሚስ የአመዘጋገብ ስርዓት መጠቀማችን የሚታወስ ነው፡፡ ሆኖም ግን በ2012 በጀት ዓመት ድጎማ በጀት የተሰጠን በመሆኑ ከኢፍሚስ አጠቃቀም ስለወጣን ከወጪ ቀሪ ጥሬ ገንዘብ፤ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ የመሳሰሉትን በኢፍሚስ መለክ ማቅረብ ባንችልም በኤክስኤል በፎፍተና በማንዋል በመጠቀም ስራዎችን ያከናወንና ሂሳብ አያያዝ የፈጸም ሲሆን በቀጣይ ከዚህ በታች ለመግለጽ እንደተሞከረው ዋና ኦዲተር በሰጠው አስተያየት መሰረት፡-
  1. MG software (የፋይናንስ ሲስተም)
  2. ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር በኢፍሚስት እና በአይቤክስ መመዝገብ እንደንችል በድጋሚ እንዲፈቀድል ጥያቄ አቅረብን በኤክስኤል የተሰራውን ዳታ ተልኮ ሂደት ማድረግ ተችሏል፡፡
- ተቋሙ በድጎማ በጀት ማለትም በሂሳብ መደብ 6412 የተሰጠና ከሁለቱም የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ኢፍሚፍስና አይቤክስ አመዘጋገብ ለመጠቀም ባለበጀት መ/ቤት ባለመሆናችንና መዝግበን ባለመጠቀማችን የተጠቀሱትን የአመዘጋገብ ስርዓቶች ልንጠቀምባቸው አልቻልንም፡፡ቢሆንም በሚቀጥለው አሰራራችንን ለማስተካከል ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር ኢፍሚስ እንዴት መጠቀም እንደምንችል የተነጋገርን ሲሆን አስፈላጊ የሆነውን የፋይናሻል ዳታ ለሚመለከተው ክፍል የተላከ ሲሆን በተጨማሪ ድርጅቱ በግልጽ ጨረታ በማውጣት የፋይናሻል ሲስተም በዘመናዊ መንገድ ለመስራት የሚያስችል MG

software ለመጠቀም በሂደትም ጎን ለጎን እየተሄደበት መሆኑን እገለጽን የሰጠን የማሻሻያ ሀሳብ የምንቀበል መሆኑን እንገልጻለን በማለት መልሰዋል፡፡

1.1.5 የኦዲተሩ አስተያት

እኛ አሰድተያየት በ2012 በጀት ዓመት ከገንዘብ ሚኒስቴር ለመ/ቤቱ የተላከው በጀት ለምን አገልግሎት እንደዋለ የሚያሳይ ድርጅቱ አጠቃላይ የሂሳብ/ፋይናንስ እንቅስቃሴውን ተቀባይነት ባለው የግዥና የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትና የሂሳብ አመዘጋገብና የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት የሚገልጽ የሂሳብ ማኑዋል በማዘጋጀት ወርሀዊ ሪፖርቶችና ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫዎች በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል የቀረበ የሂሳብ ምዝገባና የሂሳብ ሪፖርት ባለመኖሩ ምክንያት ሂሳቡን ኦዲት አድርጎ አስተያየት ለመስጠት የማያስችል በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ሆኑ አለገኘውም፡፡

በመጨረሻም በኦዲት ወቅት ስለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡